# እና በኋላማ (ለፈገግታ ያህል)

ዱሮ ትናንትም ዱሮ ነውና ዛሬም ትናንት እየሆነ ማለት። እንሰለፍ ነበር። በአርክቲክ በረዶ፣ በሞሃቢ በረሃ ቃጠሎ፣ በምድር ሰቅ ዝናብ ዶፍ፣ በአውሬ ነፋስ ክፋነት መካከል፣ መንፈሳችንን አጠንክረን በአለም ዙሪያ እንሰለፍ ነበር። ጊዜ ገንዘብ በሆነበት አለም። ከቤተሰቦቻችን ጊዜ ሰርቀን፣ የአካል ድካማችንን ችላ ብለን እንሰለፍ ነበር። ለነፃነታችን ልናለቅስ። የነፃነት ልጆች ነበርንና ነፃነትን ከሰላማዊ ሰልፍ ልንወልድ። ታስታውሱ እንደሆን በሰልፍ ሰክረን ነበር እዚህ ሰልፍ እዚያ ሻማ ማብራት . . . ታዲያ ሰልፉ ቁጭት፣ ብስጭት፣ ንዴት፣ ጉጉት፣ በመሰብሰባችን ደስታ፣ ደግሞ ጥርጣሬ፣ ስው በርከት ብሎ ሲወጣ ሞራል ከፍ፣ ሰው አንሶ ሲወጣ ብሸቀት . . . የዛሬን አያድርገውና። ዛሬ ወያኔወች የመቃብር ድንጋይ ተጭኖቻቸው የዚችን ብትጠፋ ትጥፋ ያሏትን አገር መጨረሻ ሳያዮ ቀሩ።

እና በኋላማ ጊዜ አለፈ ለፈረንጁ ሰማይ አቤት ስንል፣ የፈረንጅ መንግስት ባለፊበት አደባባይ አቤት ስንል ከፈረንጅ አደባባይ ተሰብስበን ምናልባት "ቢረዱን"፣ ምናልባት "ቢያዝኑልን"፣ ምናልባት "ልቅሶችንን ቢያግዙን"፣ ምናልባት ደግሞ " ወያኔን ጉርቤውን አንቀው ካገር ቢያባርሩልን" . . . እንዴው በተስፋና በምናልባት። ከዚህ ሁሉ ምናልባት ውስጥ ደግሞ ምናልባት የአገራችን ልጆች ተቃውሞችንን እንደ ውጭ ታዛቢ ሳይሆን እንደ ራስ ጉዳይ ተመልክተውልን፤ ምናልባት ሆ ብለው ከአገር ውጭ ያሉ ሃበሻ ሃበሾች ምናልባት ንቅል ብለው አብረውን ይቆማሉ ብለን እንሰለፍ ነበር። በሰላም ሰልፍ። እና በሆላማ ፃፍን (ነፃነታችንን እየለመንን ነበር እንዴ?) ለኮንግረስ ፃፍን፣ ለተባበሩት መንግስታት ፃፍን፣ ለአፍሪካ ህብረት ፃፍን፣ ለወያኔ መሪወች ግልፅ ደብዳቤ ፃፍን . . . ለትላልቆቹ ፈረንጆች፤ አለምን በእጃቸው መዳፍ ለጨበጡት  በነፍስ ወከፍ ፃፍን። ከዚህ ሁሉ መፃፍ መካከል ደግሞ ለአገራችን ልጆች በተለያዮ አርእስቶች የሚያነቡት አንብበው ለነፃነት መሟገታችን (ይህኛውስ መፃፍ ነፃነትን አለመለመን ነበር?) ቢገባቸውና አብረውን በፅናት ቢቆሙ ብለን ፃፍን። በአረብኛ ፃፍን፣ በእንግሊዝኛ ፃፍን፣ በፈረንሳይኛ፣ በጀርመንኛ፣ አረ በጣልያንኛም፣ በእንትንኛ ሳይቀር . . . ። የዜና አውታሮችን በየሰልፋችን ጠራን ቢቢሲን ጠራን፣ የአሜሪካ ድምፅን ጠራን፣ አጃንስ ፍራንስ ፕሬስን፣ ኬኤቢሲን፣ ኤንቢሲን፣ ሲኤንኤንን ጠራን (ጊዜ ረዝሞ ማስታወስ አቃተኝ እንጂ አልጀዚራንም ሳንጠራ ቀረን ብላችሁ ነው)። አቤት አቤት አቤት ጊዜው ሲሮጥ ወያኔወች ዛሬን ሳያዩ ተቀበሩ።

እና በኋላማ ወገኖቻችን ታሰሩብን ብለን ሰልፍ ወጣን፣ ወገኖቻችን ተገደሉብን ብለን ሰልፍ ወጣና ረሃብና በሽታን ተቃውመን። መፈክር የተፃፈባቸው ፎቶግራፎች የተለጠፋባቸው ጨርቃ ጨርቋች ተሸካክመን አደባባይ ቃላችን እስኪዘጋ አንገዛም ነፃነት ብለን በሰላም ተሰለፍን። እነሰለፍ አንሰለፍ፣ ሻማ እናብራ አናብራ፣ ሰልፉን እኛ ነን የምንጠራው አይደለም እኛ ነን እያልን ተከፋፍለን ተሟገተን፣ ተቀራርበን ተራራቅን፣ ተራርቀን ተጣላን፣ ተጣልተን ተጠላላን፣ ተጠላልተን ተጠላለፍን፣ ተጠላልፈን ተደካከመን። ጊዜ እንዴት ይሮጣል ጎበዝ?። ግፈኞቻችን የዛሬይቱ ኢትዮጵያን ሳያዩ መቃብር ገቡ። እንዳንስማማ ሳንስማማ ካገራችን ወጥተን እንዳንስማማ መስማማት አቅቶን የበላይነቱ እኛ የበታችነቱ እናንተ ተባባልን (የሰው ልጅ በሁለት ይከፈላል ደካማና ብርቱ እንዲሉ ማለት) እርስ በርስ። የጎለበትን ወይም ነፃነት የቀረበ ሲመስለን በርከት ያለው ብር ለእኛ አነስ ያለው ብር ደግሞ ለእናንተ ተባባልን። መፈክር ይሰጣችሁና አንድ ቦታ ጠርቀም ብላችሁ እንድትቆሙ ይፈቀድላችኋል (ለዚያውም ፀባያችሁ ታይቶ) ተባብለን ተደካከምን። ስብሰባ ስንጠራ በስብሰባ ላይ ስብሰባ ጠራን። ኑ አብረን እንሁን ስንል የለም እናንተ ኑ ተባባልን። ስብሰባ ኑ ግን ጥያቄ መጠየቅ አትችሉም ብለን ጠያቂነትን ከለከልን። ለምን ጥያቄ ጠየቃችሁ ብለን ተዛዛትን። ስብሰባ ላይ ሂደን ተሳደብን ተሰደብን። የሃበሻ ልጆች በተሸከፋበት ስርቻ ሁሉ እየሄድን ወረቀት እናድል አልን እነማናችሁ ተባባልን አይፈቀድም ሆነ

መልሳችን። ይጠናል ብለን መልስ ሰጠን (1966 እንደ እኛ አቆጣጠር አይደለም)። ሬዲዮ ማስታወቂያ ንገሩልን አልን ይታሰብበታል አይቻልም ሆነ መልሳችን። የታሰሩት ይፈቱ ስንል እኛ ስለቀድሞወቹ እስረኞች አያገባንም ስለዛሬወቹ ብቻ እንጅ ብለን ፍርድ አዛብተን ተላተምን። የወያኔ አስመሳይ ጉረኞችን ከጉያችን አስገብተን አቅፈን ይዘን መሪወቻችን አርገን ሌሎች ሃቀኛ ታጋዮችን አሽቀንጥረን ጥለን ብራቮ አልን። አገራችንን ነክሰው የያዙት ግፈኞች ላይ የጋራ መግለጫ እናውጣ አልን አይ የለም እኛ የራሳችንን ነው የምናወጣው ብለን መለስን። ቀደም ካለው የኢትዮጵያ ድርጅቶች ትግል ትምህርት እንቅሰም ስንል የለም ዛሬ ትናንት አይደለም አልንና የአገር ታሪክንና መማርን ችላ ብለን በማን አለብኝነት የእውር ድንብር ዳንግላሳ ረገጥን። ህዝብ “ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ” አለን አልንና ተባብረን ጉዞ ጀምረን አገር ሲፈነድቅ የግል አጀንዳወቻችን አምጥተን ህዝቡን ከዳነው። ህዝብ ተሰብሰቡ መላ አገኘን ብለን ሰው ብልኃተኝነታችንን ሊሰማ ሲመጣ መስዋዕትነታችሁም አናከብረም ብለን ሌሎቹን ነገርናቸው ብለን ተጎረርን። ማን አለ ማን ጎዳ? ራስ ጎዳ እንዲሉ ማለት። ምርጫ አልንና በጋራ ቆመን የጋራ የአገርና የህዝብ ጠላትን እናንበርክክ ተባብለን ሳንከርም ድንገት ብናሸንፍስ የሚል አዚም ይዞን ከናንተ ጋር አብረን አንቆምም ራሳቻሁን ቻሉ ብለን ተገፈታተርን። እነሱ የታሉ ድርጅታቸው እኮ ሞቶ ተቀብሯል ተባብለን አይናችን እያየ አይናችንን አናምንም ብለን በድንቁርና በቁም ተቀባበርን።

እና በኋላማ ያ የትናንቱ የረዘመ ትግል አለፈና ይኸው በትዝታ ከረጢት ውስጥ ተቋጥሮ ተቀመጠ። በየወቅቱ ጥለዉን ያለፉት ውድ ኢትዮጵያዉያን በከፈሉት መስዋእትነት እነሆ ዛሬ ፀሐይ ወጣልን። አገራችንን ይዘው በግፍ ለዘለአለም ሊገዙት ያሰቡት ወያኔወች ከተቀበሩበት መቃብር ሳይገላበጡ አንቀላፉ።

ከእምነት እስተዳር